ይድረሥ ለደብተራው

ይሕችን አጭር መጣጥፍ ልጽፍላችሁ የተነሳሁት ተአሜሪካ ብቻ ሳይሆን ተአገርቤት ጀምሮ ተእግር ሹራብ ተተሰራ ኰሥ፤ በደርግ ተቃውሞ ትግል ሆነ ሕወኀት ሐገራችንን በእግር ብረት አስሮና በረመጥ እሳት እያቃጠለ ባለበት ወቅት ጎን ለጎን ቆመን የነበረ ወንድሜ ኢሕአፓ በወሰደው ተመኢሦን ጋር የመግባባት የትግል ስልት "ዓይኔ ለአፈር" ብሎ አገሬን ነጻ ያወጣልኛል ብሎ ወደ አመነበት ድርጅት ወረደ።

እልፍ ብለን ስንገናኝ የቆጥ የባጡን አውግተንና የአገራችንን ጉዳይ አንሸራሽረን እኤም "ተው ተመለስ" ብየ እሱም "አሻፈረኝ" ብሎ እንለያያለን። ባለፈው ክረምት ተወዳጅ ቤት ጸበል ቅመሱ ተብለን ተጎኔ ተጋብዘን ተወዳጆቻችን ስንቀላቀል በግብር ቤቱ ያአብሮ አደግ ወንድሜ ተገበናው ዓናት ተቀምጦ እንደ ብርቱ መምሕር የተሰበሰበውን ሁሉ ክንዱን እያነሳ "የኢሐዴግ መንግስት ኢሄ ለኔ ስትለው ያንተው ብሎ በቃኝ ስትለው በሞትኩት እያለ በአፍ የሚሞጅር አስተዳደር ነው" ምክሬን ስሙ እያለ የተሰበስበውን ሰው "ቀኑ ደርሶል" እንደሚል ባሕታዊ ሲነዘንዘው ገረመምኩት።

ጎኔ ቀስ ብላ "ይሄማ ወዳጅሕ አይደል" ብትለኝ በትር እንደመታው አውሬ "እርግኝ" አስባለችኝ። ተቅርቡ ስሰማ ወዳጄ መሬት ተመርቻለሁ ቤት ልሰራነው እያለ የሞኾ ቃል እንደውም የኢሐዴግ ቆንስል በአበሻ ምግብ ቤት እጅ ሲነሳ አይተናል ቢሉኝ ተሰው ተጣልቼ ጣብያ ልወርድ የኢትዩጵያ አምላክ ነው ያወጣኝ። አሁን በአይኔ በብረቱ አሳየኝ በጆሮዬም ዶለልኝ። ጅብ እንደነከሰ አሕያ መንጋጋዬ አልላቀቅ ብሎ በንዴት እሕል ሳልቀምስ ጎኔን አስቀድሜ ተቤቴ ገባሁ።

ማልዶ ሲመሽ ወይ አምላኬ ወይ ነዶ እያልሁ ያን ወዳጄና ወንድሜን ሳስብ ከረምኩኝ በሽውታም ተአገር ቤት እንደገባም ተረዳሁ አይ እንግዲህ ደርሶ ተቀናው ይሁን እንጂ ምን አረጋለሁ ብዬ ዳግመኛ ላላስበው ተአናቴ መንቅሬ ላወጣው ታዕምሮዬ ትግል ገጥሜ ማቸነፍ ተስኖኝ "ወግድ" ብዬ ማላዘኔን ቀጠልኩ።

በቅርቡ ሕወኀት በቅንጅት መሪዎች በነጻ ጋዜጠኞች እና በሲቪክ መሪዎች ላይ በራሱ በሚተዳደረው የፌንጣ ፍርድ ቤት አማካኝነት ፍርደ ገምድሉን በሰጠ ማግስት ተቤቴ ያለች ስልክ እሪታዋን አሰማች ተአጠገቦ የማትጠፋው ጎኔ መነጋገሪያውን አንስታ "ሐሎ" ብላ ሳትጨርስ ወዴኔ መነጋገሪያውን አምዘገዘገችው ስልኩን ሳልቀበል "ማነው" ብዬ ብቆጣ "ስም አልገለጡልኝም" አለች ጎኔ ሳቅ ባፈነው ጉጥጫ "ማ ልበል" አልኩኝ መነጋገሪያውን ተጆሮዬ ደቅኜ።

ተስታር ባክስ ቡናውን ጎንጨት እያለ ተግርጌ ተቀምጦ በር በሩን ሲመለከት በመስኮት በኩል አጨውልቄ ታዘብኩት "መን ይሆን ጉዱ" ብየ ታሰበኝ። ተሰላም ልውውጥ በኋላ "ምነው ወገኔ በሰላም ነው?" ብዬ ጠየኩ "ምን ሰላም አለ" ብሎ አንገቱን ደፍቶ ተአግር ቤት ወርጄ ነበር ቤትሰብ ወዳጅ ደግ ነው አገር ግና ደግ አይደለም አንበጣና የሰው ተባይ ወሮታል። ቤት ይጠብቁ ተብሎ አይጥ የማይበላ ድመት አምጥተው ድመቱም የአይጥ እስረኛ ሆኖ ቀረ። ዛሬ አንተን የጠራሁሕ ተይቅርታህ ሌላ ተልቤ ልነግርሕ የፈለግሁት አገራችንን ነጻ የሚያወጣ ድመት ሳይሆን ነብር ብቻ ነው እንደ እኔ እንደኔ ያ ነብር ኢሕአፓ ብቻ ነው ብሎ ተነፈስ።